ለገጣሚያን፡ ለሶስተኛው ዓመት የደብተራው የሥነ-ጽሑፍ ቀን የተሳትፎ ጥሪ

# ሰብአዊ መብትና ደብዛቸው የጠፉ ኢትዮጵያዊያን ዕጣ ፈንታ

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሩና የመብቱ ባለቤት ለመሆን በሚያካሂደው ትግል በግንባር ቀደምነት ታግሎ ሲያታግል ከዘረኛው የወያኔ እጅ ወድቆ ላለፉት 20 ዓመታት ደብዛው በጠፋው ደብተራው (ጸጋዬ ገብረመድህን) ስም የተሰየመው የስነ-ጽሑፍ ቀን ዘንድሮም ለሶስተኛ ጊዜ ተከብሮ ይውላል። ለትግሉ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ለማበርከት በሕዝብ መገናኛው ዘርፍ እየሰሩ ያሉት አሲምባ የውይይት መድረክ፣ ደብተራው ድረ-ገፅ እና ፍኖተ-ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ በትብብር የሚያዘጋጁት ይኸው "የደብተራው የሥነ-ጽሑፍ ቀን" ተከብሮ የሚውለው ሚያዝያ 22፣ 2003 ዓ. ም. (30 April 2011) ነው።

የዕለቱ ዋና ጭብጥ (theme) የሚሆነውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት ረጅም ዓመታት ባካሄደው መራር ትግል መስዋዕትነት ከፍለው የወደቁና ደብዛቸው የጠፉ የሕዝብ ልጆችን መዘከር ይሆናል። የሕዝብ ልጆችን ትግል ከሚዘክሩ፣ ወያኔም አፍኖ ያጠፋቸውን የሕዝብ ልጆች የት እንዳደረሳቸው ይፋ እንዲያደርግ ስለተካሄደው ዓለማቀፋዊ ጥረት እና ስላጋጠሙ ችግሮች ከሚያስገነዝቡ ሌሎች ዝግጅቶች ጋር በተጓዳኝነት የተለያዩ ግጥሞችንም ለማቅረብ ታስቧል። ኪነጥበብ ኪነጥበብ የሚሆነው እውነትን፣ ሕይወትንና ውበትን በአንድነት አዋህዶ ሲያቀርብ ነውና፣ ገጣሚያን የሕዝብ ልጆችን ለመዘከር ብዕራቸው እንደማይገደውም ሙሉ እምነታችን ነው።

**ሰብአዊ መብትና ደብዛቸው የጠፉ ኢትዮጵያዊያን ዕጣ ፈንታ** በሚለው የዕለቱ ጭብጥ ላይ ያተኮሩና ከሶስት ገጽ ያልበለጡ ግጥሞቻቸውን በ info@debteraw.com ኢሜል አድራሻ እስከ ሚያዝያ 16 ቀን 2003 ዓ. ም. (24 April 2011) ድረስ እንዲልኩልን ገጣሚያንን በአክብሮት እንጋብዛለን። ከሚላኩልን ግጥሞች ውስጥ በዳኝነት በተሰየሙ ሶስት ደራሲያን የሚመረጡት ሥራዎች በዕለቱ ለዝግጅቱ ተዳሚዎች ይነበባሉ።

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!

ደብዛቸው የጠፋው ታጋዮች የት ደረሱ ብለን በጋራ ጥያቄያችንን እናሰማ!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ያቸንፋል!

የደብተራው የሥነ-ጽሑፍ ቀን አዘጋጅ ኮሚቴ